# የዘካህ ህግጋት

## አጭር ማብራርያ

## በኢልያስ አህመድ

**ዘካህ** የስርወ-ቃሉ ቋንቋዊ ትርጉም፦ "መብዛት"፣ "ማደግ"፣ "መጨመር" እንዲሁም "ማወደስ"ና "(ከጉድፈት) ማጥራት"ን የሚያመለክት ነው፡፡

**የዘካህ ሸሪዓዊ መልእክት** ደግሞ፦ በየተወሰኑ ጊዜያት ከተወሰኑ የንብረት ዓይነቶች ተቆንጥሮ ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሉች በግዴታነት የሚሰጥ የተገደበ ወጪ ነው፡፡

የዘካህ ድንጋጌ እንደሌሎቹ መለኮታዊ ህግጋት ሁሉ ከአምልኮ ዘርፍነቱ ባሻገር ድንቅ፣ ብርቅና ፅድቅ ጥበቦችንና ዓላማዎችን ያነገበ ነው፡፡ ሰዎች ሲረዱቸው ከሚችሏቸው ግለሰባዊና ማሕበራዊ ጥቅሞቹና የመፍትሄነት ገፅታዎቹ መካከል፦

1. ለችግረኞች መረጃ መሆኑ፣

2. ለድሆች መቋቋሚያ መሆኑ፣

3. በእምነት ላይ የተመሠረተ የወዳጅነትና የወንድማማችነት ትስስርን ማጥበቁ፣

4. ስብዕናን ከስስትና ከንፉግነት ማፅዳቱ፣

5. ድሆች ለሀብታሞች ያላቸውን ምልከታ ከምቀኝነት ማጥራቱ

6. በድህነት ምክንያት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መገደቡ

7. ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቅል ኢስላማዊ ጉዳዮችን

ለማቀላጠፍ ምክንያት መሆኑና፣

8. የንብረት በረከት ማስከተሉ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## በኢስላም ያለው ደረጃና ብይን

ዘካህ ኢስላም ከተገነባባቸው አምስቱ መሠረቶች 3ኛው ሲሆን ለዘካህ ብቁ የሆነ ገንዘብ ያለው ማንኛውም ሙስሊም በግዴታነት ዘካህ ማውጣት እንዳለበት በሙስሊሞች መካከል በጥቅሉ ያለምንም ውዝግብ የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡ ይህንን የሚያስገነዝቡት ቁርአናዊና ሀዲሳዊ አስተምህሮቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ፦

◄ وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ [البقرة: 110]

► «ሰላትንም አቋቁሙ፤ ዘካህንም ስጡ!»

◄ فَإِنْ تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَإِخْوَانُكُمْ فِي الدِّينِ [التوبة:11]

▶«(ተፀፀትው) ከተመለሱ ሰላትንም ካቋቋሙ ዘካህንም ከሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው።»

◀ عَنْ ابْنِ عُمَرَ – رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا – قَالَ : قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ﷺ: «بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ : شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالْحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ» متفق عليه.

▶ዓብዱላህ' ብኑ ዑመር የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል አሉ፡-

« ኢስላም በአምስት ነገሮች ላይ ተገነባ፡- ከአላህ በቀር አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ማቋቋም፣ ዘካን መስጠት፣ ሐጅ ማድረግና ረመዳንን መፆም»(1)

**ዘካን ወጪ የማያደርግ ባለሀብቶች ሁለት ዓይነት ናቸው:-**

1ኛው ዓይነት፦ የዘካህን ግዴታነት ከማስተባበል ወይም ከኩፋትና ከትዕቢት በመነጨ እምቢተኝነት የተነሳ የሚነፍግ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ከኢስላም ምንም ድርሻ የሌለው ከሀዲ ስለመሆኑ ጥርጥር የለም።

2ኛው ደግሞ፦ ግዴታነቱን ሳያስተባብል በስስት ወይም በመዘናጋት የተነሳ የሚነፍግ ሲሆን ስእንዲህ ዓይነቱ የሚሰጠውን ብይን አስመልክቶ የኢስላም ሲቃውንት ሁለት አመለካከቶች አሏቸው፤

ጥቂቶቹ ይኸኛው እንደመጀመሪያው ከሀዲ መሆኑን ሲናገሩ ብዙሃኑ ግን ወንጀሉ ከባድ ቢሆንም ከኢስላም የሚያስወጣው የክህደት ደረጃ

(1) አል-ቡኻሪ (8)፣ ሙስሊም (16)

አይደርስም ይላሉ:: መልዕክተኛው ዘካህን የነፈገ በፍርዱ ቀን የሚያጋጥመውን ቅጣት በጠቀሱ ጊዜ፦

◄ «..فيُرى سبيلَه؛ إما إلى الجنة، وإما إلى النار!» رواه مسلم

►«...ከዚያም መንገዱን ይመለከታል (ይጠቆማል)፤ ወይ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት!»(1) ማለታቸው የአብዛኛውን አቋም ይደግፋል::

## ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው መስፈርቶች

የሚከተሉት መሥፈርቶች በሙሉ ካልተሟሉ በስተቀር ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም፤

1. ሙስሊም መሆን ፦ ሙስሊም ያልሆነ ሰው ከዘካህ በፊት ሊያሟላቸው የሚገባ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ስላሉ ዘካህ መስጠት እንደሙስሊም ግዴታ ይሆንበታል አይባልም:: ነገር ግን ሙስሊም ባለመሆኑና ዘካህን ጨምሮ ሌሎች ኢስላማዊ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ፣ እንዲሁም በዝርዝር ጥፋቶቹ መንስኤነት የወዲያኛው ዓለም ቅጣት እንደሚነባበርበት የሚጠቁሙ ቁርአናዊ መረጃዎች አሉ::

2. ከባርነት ነፃ መሆን ፦ ባሪያም በእጁ ያለው ገንዘብም የጌታው ንብረት ናቸውና ዘካህ የማውጣቱ ሃላፊነት ሱሲውን ሳይሆን አለቃውን የተመለከተ ይሆናል::

(1) ሙስሊም (987)

3. **ሙሉ ባለቤትነት** ፦ እንደ «ወቅፍ» ያለ ውስን ባለቤት የሌለው ንብረት ላይ ዘካህ አይደነገግም። በውል ባልተረጋገጠ ባለቤትነት ላይ ያለው ፍርድም ተመሳሳይ ነው።

4. **ንብረቱ «ኒሷብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛው መጠን) መድረሱ**፦ ይህ መጠን እንደንብረቱ አይነት ሊለያይ ይችላል።

5. **ንብረቱ በባለቤቱ ይዞታ ስር ከ«ኒሷብ» ሳይጎድል በጨረቃ አቆጣጠር አንድ ዓመት መቆየቱ** ፦ ሆኖም ይህ መሥፈርት ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ሦስት ነገሮች አሉ፦

   አንደኛው፦ አዝርዕትና ብቅሎች - የዘካ ጊዜያቸው የአዝመራ ወቅት ነውና።

   ሁለተኛው፦ ቀድሚያ ከነበሩ ግመሎች፣ ከብቶች ወይም በጎችና ፍየሎች የተወለዱ አዳዲስ ግልገሎች፤

   ሦስተኛው፦ የንግድ ትርፍ፤

እነዚህ ሦስት የንብረት ዓይነቶች ዓመት ባይሞላቸውም ሌሎች መስፈርቶች ከተሟሉ የዘካህ ግዴታ ይመለከታቸዋል።

► ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ለአቅመ አዳም መድረስና የአእምሮ ጤናማነት ያልተጠቀሰበት ምክንያት ፦ ህፃን ልጆች ወይም አእምሮአቸው የታወከ ግለሰቦች ምንም እንኳን ሸሪዓዊ ግዴታዎች በቀጥታ ባይመለከቷቸውም ንብረታቸው ግን «ኒሷብ» እስከደረሰ ድረስ በንብረትነቱ ብቻ ዘካህ ሊወጣለት ስለሚገባ ነው፤

የዘካህ ግዴታነት ከንብረቱ እንጂ ከባለንብረቱ ጋር ተያያዥነት የለውምና:: ይህ የብዙሀኑ ሊቃውንት አቋም ሲሆን ይህንንም የሚጠቁሙ ንግግሮች ከተለያዩ ሰሃቦች ተዘግበዋል::

## የዘካህ ንብረቶች

## (ዘካህ ግዴታ የሚሆንባቸው ንብረቶች)

ዘካህ ግዴታ የሚሆነው በጥቅሉ በአራት የንብረት አይነቶች ላይ ነው፤ እነሱም ፦

❶- የሚታረቡ ግመሎች፣(የቀንድ) ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች፤

❷- የእርሻ አዝርእትና ሰብሎች፤

❸- የዋጋ ተመን የሆኑ ንብረቶች ማለትም ወርቅና ብር (silver) እንዲሁም የዘመናችን የገንዘብ ኖቶች፤

❹- ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውምሸቀጥና ሰቃ ተመን፤

ዝርዝሩን እነሆ!

# 1-የሚሩቡ ግመሎች፣ የቀንድ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች

ከነኚህ እንስሶች ዘካህን መስጠት ግዴታ የሚሆነው በፊት ከተጠቀሱት ጥቅል የዘካህ መስፈርቶች ጋር ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ሲጨመሩ ነው፤ እነሱም፦

1ኛ- አመቱን ሙሉ ወይም የአመቱን አብዛኛውን ክፍል ሙብላቸው በግጦሽ ስምሪት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። ስለሆነም በአብዛኛው የአመቱ ክፍል በባለንብረቱ ወጪ የሚዘጋጅ የመኖ ቀለብ የሚመገቡ ከሆነ የዘካህ ግዴታ አይመለከታቸውም ማለት ነው።

2ኛ- እንስሶቹ ለርባታ፣ ለወተት ወይም ለማደለብ ዕቅድ የተያዙ መሆናቸው ነው። እናም በዋነኛነት ለሥራ የታሰቡ ከሆነ ዘካህ ማውጣት የግድ አይልም ማለት ነው። እንደምሳሌ፦ አንድ ግለሰብ ለሸክም ሥራ የሚያከራያቸው ግመሎች ወይም ለእርሻ የሚያጠምዳቸው በሬዎች ቢኖሩት ቁጥራቸው ቢበዛ እንኳ ከነርሱ ዘካህ ማውጣቱ ግዴታ አይሆንም። ለሽያጭ የተዘጋጁ ከሆነ ደግሞ የዘካ አወጣጥ መስፈርቱና ህጉ ወደፊት እንደሚገለፀው ለየት ይላል።

3ኛ- እንስሶቹ በሸሪዓ የተገደበላቸውን «ኒሳብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ ቁጥር) የደረሱ ሲሆኑ ይገባል። ይህም እንደ እንስሳው ዓይነት የሚለያይ ሲሆን ዝርዝሩን ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ማስተዋል ይቻላል።

# የግመል ዘካህ አወጣጥ

| የርቢ ግመሎቹ ብዛት | | ለዘካህ የሚወጣው | |
|---|---|---|---|
| ከ | እስከ | ዓይነት | ብዛት |
| 1 | 4 | - | 0 |
| 5 | 9 | በግ ወይም ፍየል | 1 |
| 10 | 14 | በጎች ወይም ፍየሎች | 2 |
| 15 | 19 | በጎች ወይም ፍየሎች | 3 |
| 20 | 24 | በጎች ወይም ፍየሎች | 4 |
| 25 | 35 | አንድ አመት የሞላት ሴት ግመል(1) | 1 |
| 36 | 45 | ሁለት አመት የሞላት ሴት ግመል | 1 |
| 46 | 60 | ሦስት አመት የሞላት ሴት ግመል | 1 |

(1) እዚህ ላይ ባለአንድ አመት **ሴት** ግመል ሳይኖረው ባለሁለት አመት **ወንድ** ያለው ያንኑ መስጠት ይችላል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 61 | 75 | አራት አመት የሞላት ሴት ግመል | 1 |
| 76 | 90 | ሁለት አመት የሞላቸው ሴት ግመሎች | 2 |
| 91 | 120 | ሦስት አመት የሞላቸው ሴት ግመሎች | 2 |

➔ ከ120 በላይ ያለው ለእያንዳንዱ 40 ግመል ሁለት አመት የሞላት ሴት ግመል፤ ለእያንዳንዱ 50 ግመል ደግሞ ሦስት አመት የሞላት ሴት ግመል ይከፍላል።

ለምሳሌ፦

- 130 ግመሎች ያሉት ሰው፦

130 = 40 + 40 + 50

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| = | አንድ የሁለት አመት ሴት ግመል | + | አንድ የሁለት አመት ሴት ግመል | + | አንድ የሦስት አመት ሴት ግመል |

ይህ እስከ 139 አይቀየርም!

- 140 ግመሎች ያለው ሰው፦

140 = 50 + 50 + 40

=

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አንድ የሣስት አመት ሴት ግመል | + | አንድ የሣስት አመት ሴት ግመል | + | አንድ የሁለት አመት ሴት ግመል |

ይህም እስከ 149 ድረስ አይቀየርም!

- 200 ግመሎች ያሉት፦

200 = 50 x 4 = አራት ባለ ሶስት ዓመት ሴት ግመሎች

= 40 x 5 = አምስት ባለ ሁለት ዓመት ሴት ግመሎች

ስለዚህ ከሁለቱ መንገዶች በመረጠው ዘካህ ያወጣል ማለት ነው፡፡

➔ ከተገደቡት የዕድሜ ደረጃዎች ያነሰ ወይም የበለጠ ብቻ ያለው ባለ ግመል በእያንዳንዱ የአመት ልዩነት ሁለት በጎች ወይም ፍየሎችን አሊያም 20 ዲርሃም ይከፍላል ወይም ይቀበላል፡፡(1)

☸☸☸

(1) 20 ዲርሃም ወደ 59.5 ግራም የሚመዝን ብር (silver) ነው፡፡

# የቀንድ ከብት (የላምና የበሬ) ዘካህ አወጣጥ

ለእያንዳንዱ 30 ከብት አንድ አመት የሞላው/ት አንድ ወንድ ወይም ሴት ጥጃ ለእያንዳንዱ አርባ ደግሞ ሁለት አመት የሞላት ሴት ከብት ያወጣል።

| የርቢ ከብቶቹ ብዛት | | ለዘካህ የሚወጣው | |
|---|---|---|---|
| ከ | እስከ | ዓይነት | ብዛት |
| 1 | 29 | - | 0 |
| 30 | 39 | አመት የሞላው/ት ጥጃ | 1 |
| 40 | 59 | ሁለት አመት የሞላት ጊደር | 1 |
| 60 | 69 | አመት የሞላቸው ጥጆች | 2 |
| 70 | 79 | አንድ ባለ አንድ አመት ጥጃና አንድ ባለ ሁለት አመት ጊደር | 2 |

በዚህ መልኩ ይቀጥላል፤

ስምሣሌ፦

- 80 ከብቶች ያለው ሰው፦

80 = 40 + 40

= ባለ ሁለት አመት ጊደር + አንድ ባለሁለት አመት ጊደር

= 2 ባለ ሁለት አመት

እስከ 89 አይቀየርም!

- 90 ያለው ሰው:-

90 = 3 x 30 = 3 ባለ አንድ አመት ጥጆች

እስከ 99 አይቀየርም!

- መቶ ያለው ሰው:-

100 = 40 + 30 + 30

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| = | አንድ የሁለት አመት ጊደር | + | ባለአንድ አመት ጥጃ | + | ባለአንድ አመት ጥጃ |

☸☸☸

# የበግና የፍየል ዘካህ አወጣጥ

| የርቢ በጎቹ/ፍየሎቹ ብዛት | | ለዘካህ የሚሰጠው | |
|---|---|---|---|
| ከ | እስከ | ዓይነት | ብዛት |
| 1 | 39 | - | 0 |
| 40 | 120 | በግ ወይም ፍየል | 1 |
| 121 | 200 | በጎች ወይም ፍየሎች | 2 |
| 201 | 399 | በጎች ወይም ፍየሎች | 3 |

ከዚህ በኋላ ባለው ቁጥር በ100 በጎች/ፍየሎች ሂሳብ አንድ በግ/ፍየል ይወጣል:: ለምሳሌ:-

- 400 በግ ያለው ሰው 4 በግ/ፍየል ያወጣል::

ይህ እስከ 499 አይቀየርም!

- 500 ያለው አምስት ያወጣል::

➔ ለዘካህ ወጪ የሚደረጉት በጎች ቢያንስ 6 ወር ፤ ፍየሎቹ ደግሞ አመት የሞላቸው ሲሆኑ እንድሚገባ በርካታ ዑለማዎች የሚናገሩ ሲሆን የተለየ አቋም ያላቸው ሲቃውንትም አሉ::

## የእንስሶቹን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመሪያዎች

1. ከአንድ በላይ ባለንብረት ያላቸው የዘካህ ከብቶች በአንድ በረት እያደሩ በአንድ የጋራ እረኛ የሚሠማሩ ከሆነ እንደ አንድ ሰው ንብረት ይታሰባሉ:: የዛካህ ህጉም ይህንን የተከተለ ይሆናል::

   ለምሣሌ:- ሁለት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው 40 በጎች ቢኖሯቸውና ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ቢደባልቋቸው ዘካህ የሚያወጡት 1 በግ ብቻ ይሆናል:: እያንዳንዳቸው 20 ቢኖሩቸውም እንደዚሁ አንድ በግ መስጠት ይኖርባቸዋል:: ለዘካህ የምትሠጠው በግ ከአንደኛው ንብረት ትወሰድና ከሌላኛው የዋጋዋን ግማሽ ይቀበላል::

2. ከሦስት ሁኔታዎች በስተቀር ወንድ ከብቶችን ማውጣት አይቻልም:-

   ❶ አመት የሞላት ሴት ግመል ያጣ ባለሁለት አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል::

   ❷ በሬና ላም ያለው ባለአንድ አመት ወንድ መስጠት ይፈቀድለታል::

   ❸ ሴት ከብት ጭራሽ የሌለው ከሆነ ወንድ ማውጣቱ ከችግር አንጻር እንደሚፈቀድለት በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ::

3. ለዘካህ የሚሰጡት ከብቶች በጣም ወድ የሆኑት ወይም በጣም ደተራከሱት ሳይሆን መለስተኛ የሆኑት ናቸው::

4. የከብቶቹ ቁጥር «ኒሷብ» ከደረሰ በኋላ የሚወለዱ ጥጆችና ግልገሎች ዓመት ባይሞላቸውም በዘካህ ሂሳብ ውስጥ ይደመራሉ::

   ለምሳሌ:- 120 በጎች በይዞታው ስር ያሉ ግለሰብ በ11ኛው ወር አንዲት ግልገል ብትወለድለት/በት(!) ከአንድ ወር በኋላ ሁለት በጎችን ለዘካህ ያቀርባል::

## 2- የእርሻ አዝረዕትና ሰብሎች

የእርሻ ባለቤት የሆነ ግለሰብ አዝመራ በተሰበሰበ ጊዜ ከፊሉን ለዘካህ ወጪ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ የሚሆነው እንደሌሎች የንብረት ዓይነቶች ዓመት ጠብቆ ሳይሆን በአዝመራ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

የአዝርዕትና የጥራጥሬ ዘካህ ግዴታነቱ የሚፀድቀው ከዚህ በፊት ከተጠቀሱት የዘካህ ጥቅል መስፈርቶች ጋር ሌሎች ቅድም ሁኔታዎች ሲታከሉ ነው፡፡

እነሱም፦

1. አዝርዕቱ በመስፈሪያ የሚለካ ወይም መለካት የሚችል መሆኑ፣
2. በመሠረታዊ ምግብነት የሚያገለግሉና ታጉረው ሊቆዩ የሚችሉ መሆናቸው(1)፣

➲ በእነዚህ ሁለት መሥፈርቶች መሠረት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ምስር፣ ተምር፣ ዘቢብ ካሉ እህሎች፣ ጥራጥሬዎችና ፍሬዎች ዘካህ ሊወጣ እንደሚገባ እንረዳለን፤ በአንፃሩ ደግሞ እንደ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣ ጎመንና ሽንኩሩ ባሉት ቀጠላ ቀጠሎችና ፍራፍሬዎች ላይ ዘካ ግዴታ እንደማይሆን እንገነዘባለን፡፡

3. አዝርዕቶቹና ሰብሎቹ በግለሰቡ ይዞታ ስር ሆነው ለአዝመራ መድረሳቸው፣

---

(1) ይህንን መስፈርት የማይቀበሉ በርካታ ሊቃውንት አሉ!

ለምሳሌ፦ አዝመራው ከደረሰ በኋላ (ባይሰበሰብ እንኳ) አዝርዕቱን በስጦታ ወይም በግዢ፣ አሊያም በውርስ ያገኘ ሰው ዘካውን የማውጣት ግዴታ የለበትም፤ ግዴታው በቀድሞው ባለቤት ላይ ይሆናልና! ለአዝመራ ከመድረሱ በፊት የተረከበ እንደሆነ ግን አዝመራው ሲደርስ ግዴታው ይመለከተዋል።

4. አዝርዕቱ ከተወቃ በኋላ መጠኑ ቢያንስ 1200 የሁለት ዕጅ ስፍር መሙላቱ፣ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሸሪዓዊ ገደብ ስፍርን የተመረኮዘ እንጂ ክብደቱን የተመለከተ እንዳልሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። የተከበረት መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፦

◀ «ليس فيما دون خمسة أوسق صدقة»

▶ «ከአምስት "አውሱቅ" በታች ሰደቃ የለም»[1]

- 1 ወሰቅ = 60 ሷዕ[2]፤ 1 ሷዕ = 4 የሁለት ዕጅ እፍኞች
- 5 አውሱቅ = 5x60ሷዕ = 300ሷዕ = 300x4 እፍኞች = 1200 እፍኞች

ይህም ከሞላ ጎደል በደህና የስንዴ ስፍር ሲለካ በትንሹ 612 ኪ.ግ አካባቢ ይመዝናል። ሆኖም የስፍሩ ክብደት እንደየእህሉ አይነት የሚለያይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

---

(1) አል-ቡኻሪ(1447)፣ ሙስሊም(979)(980)
(2) በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ነው።

➔ እነሱ እጅ በእጅ ባይሰፈር እንኳ ከአዝመራው በፊት ለምድ ባላቸው ታማኝ ሰዎች መጠኑ ሲገመት እንደሚችል ብዙሀኑ ሲቃውንት ይስማማሉ፡፡ ታዲያ በዚህ መልኩ ሲሰላ 1/3ኛውን ወይም 1/4ኛውን ከሂሳቡ ማቃለል እንደሚገባ የሚጠቁም ሐዲሥ ቢኖርም በርካታ ሊቃውንት ዘገባው ጠንካራ እንዳልሆነ ያወሳሉ፡፡

❁❁❁

## ለዘካህ ወጪ የሚሆነው መጠን

አዝርዕቱ ከላይ የተጠቀሰው የስፍር መጠን ያህል ከደረሰ ተሰፍሮ ወጪ የሚሆነው የዘካህ መጠን እንደሚከተለው ይገለፃል፦

➢ እርሻው በዝናብ፣ በወንዝ ወይም በመስኖና በመሳሰሉት ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ ከሆነ ከተሰበሰበው አንድ አስረኛው (10%) ለዘካህ ይሰጣል፤ እነዚህ ላይ የሚታየው ውሃ ለማጠጣት ተደጋጋሚ ልፋት አለመኖሩ ነውና!

➢ ማሳው የገበሬውን ተደጋጋሚ ልፋት በሚጠይቁ የውሃ ማጠጫ ዘዴዎች ውሃ የሚያገኝ እንደሆነ ግን አንድ ሃያኛውን (5%) ብቻ ወጪ ያደርጋል፡፡ ይህ ውሃን በተለያዩ ዘዴዎች በመቅዳት፣ ወይም በዘመናዊ መሣሪያዎች ወደ እርሻው በማስተላለፍ የሚካሄደውን የማጠጣት ስልት ያካትታል፡፡

## የአዝርዕቱን ዘካህ የተመለከቱ ጥቅል መመሪያዎች

- የተለያዩ የእህልና የአዝርዕት ዓይነቶች ለየብቻ ሲሰፈሩ በተናጠል «ኒሷብ» ካልደረሱ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም፡፡

- በኪራይ ወይም በተለየ ውል በሌላ ሰው መሬት ላይ እህል የዘራ ግለሰብ የዘካህ ግዴታ ይመለከተዋል፤ የእህሉ ባለቤት እርሱ ነውና፡፡ የመሬቱን ባለቤት የአዝርዕቱ ዘካህ አይመለከተውም፡፡

# 3-እንደ ወርቅና ብር ያሉ የዋጋ ተመኖች ዘካህ

የወርቅና የብር ማዕድኖች በቀድሞው ዘመን ዋነኛ መገበያያና የተመን መስኪያ ሆነው ቆይተዋል። ስለሆነም ለዘካህ የደረሰ የወርቅ ወይም የብር (ሲልቨር) መጠን ኖሮት በጨረቃ አቆጣጠር አመት ያሳለፈ ሙስሊም የተወሰነውን ያህል ወጪ ማድረግ እንደሚገባው በሸሪዓችን ፀድቋል።

- **ወርቅን አስመልክቶ** ፦ ቢያንስ 20 ዲናር (ሚሥቃል) ያለው ሰው ከአመት በኋላ 1/40ኛውን (ወይም 2.5%)ለዘካህ ወጪ ማድረግ አለበት።

  20 ዲናር (ሚሥቃል) በዘመናችን መስኪያዎች ሲገለፅ እንደሚከተለው ይሆናል፦

  1 ዲናር ወርቅ = 4.25 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)

  20 ዲናር = 85 ግራም

  ✸ እናም የወርቅ «ኒሷብ» (ዘካህ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ መጠን) = **85 ግራም** ነው ማለት ነው።

- **የብር ማዕድንን አስመልክቶ** ፦ ቢያንስ 200 ዲርሀም ያለው ሰው በአመቱ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካ ወጪ ማድረግ ይኖርበታል።

  200 ዲርሃም በዘመናችን መስኪያዎች ሲገለፅ እንዲሚከተለው ይሆናል፦

  1 ዲርሃም = 2.975 ግራም (በብዙሀኑ አቋም)

  200 ዲርሀም = 595 ግራም

✸ እናም የብር (ሲልቨር) «ኒሳብ» **595 ግራም** ይሆናል ማለት ነው።

➔ከሴሳ ማዕድን ጋር የተቀየጠ ወርቅ ወይም ብር ቀይጡ አጠዛኙን መጠን የያዘ እንደሆነ ወርቁ ወይም ብሩ ለብቻው የሚኖረው የተጣራ ክብደት «ኒሷብ» ካልደረሰ ዘካህ ማውጣት ግዴታ አይሆንም:: የቀይጡ መጠን በጣም አነስተኛ ከሆነ ግን የወርቁ/የብሩ የተጣራ ክብደት ለብቻው የኒሷብ መጠን ባይኖረው እንኳ በድምሩ የኒሷብ መጠን ከደረሰ ከአጠቃላዩ ዘካህ ማውጣት የግድ እንደሆነ የሚናገሩ ሊቃውንት አሉ:: ሌሎች ደግሞ እንደመጀመሪያው የተጣራው ንጹህ ወርቅ/ብር ለብቻው እንደሚሰላ ይናገራሉ፤ በዚሁ መሠረት፦

ባለ 24 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 85 ግራም

ባለ 21 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 97.14 ግራም

ባለ 18 ካራት ወርቅ ኒሷብ = 113.3 ግራም

➔ ወርቅ እና ብር የተለያዩ ሸሪዓዊ ብይኖች ያሏቸው በመሆኑ በዘካህ ላይ የተለያየ ሂሣብ ይሰላላቸዋል እንጂ አንድ ላይ አይደበሉም ::

➔ በሸሪዓ በተፈቀደ መልኩ እንደ ጌጥ የሚያገለግል የሴቶች ወርቅንና ብርን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው:: ጥቅል ቁርአናዊና ሀዲሣዊ አስረጆች የሚደግፉት አቋም መጠኑ "ኒሷብ" እስከደረሰ ድረስ ዘካህ በየዓመቱ ማውጣቱ የግድ መሆኑን ነው::

☸☸☸

# የገንዘብ ዘካህ

በዘመናችን የዋጋ ተመንነትን ተከቶ የሚገኘው የገንዘብ ኖትን አነሳስና ታሪካዊ ሂደት የተመለከቱ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሲሠጠው የሚችለውን ሸሪዓዊ ብይን አስመልክትም የተለያዩ አስተያየቶች ተሠንዝረዋል፡፡ ጻፊ ግን የኢኮኖሚው ዓለም ተጨባጭ ሂደት የሚያስረዳው የገንዘብ ኖት የግብይት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑ በተዘዋዋሪ ከወርቅና ከብር ጋር ቢያመሳስለውም <u>ራሱን የቻለ የዋጋ ተመን</u> መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም «ኒሷብ» የደረሰ የገንዘብ መጠን ኖሮት አመት ያሳለፈ ሙስሊም ከገንዘቡ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ መክፈሉ የግድ ይሆናል፡፡

ታዲያ ዘካ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ የገንዘብ መጠን (ኒሷብ) የሚገደብበት መሠረት የወርቅ ዋጋ ወይስ የብር? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ብዙሀኑ የዘመናችን ሊቃውንት የመረጡት ሚዛን ጾሬ አቋም በወቅቱ ከሁለቱ የኒሷብ ዋጋዎች አነስተኛ በሆነው ላይ እንደሚሆን ነው፡፡

ለምሳሌ፦➢ ዘካህ በሚወጣበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 500 ብር ቢሆን ይህንን በ85 ስናበዛው የወርቅ ኒሷብ ዋጋ ይሰጠናል፦

➲ 500 x 85 = 42,500 ብር ይሆናል፤

➢ የብር (ሲልቨር) ዋጋ ደግሞ በግራም 25 ብር ቢሆን ይህንን በ595 ስናበዛው የኒሷቡን ዋጋ ይሠጠናል፦

➲ 25 x 595 = 14,875 ይሆናል፤

ይህ ውጤት ከወርቁ የኒሷብ ዋጋ ያንሳል። በመሆኑም የገንዘብ ኖት ዘካህ በብር ዋጋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ ያለው ተመን የሚያሳየንም የብር ኒሷብ ዋጋ ከወርቅ ኒሷብ ዋጋ እጅግ እንደሚያንስ ስለሆነ <u>ቢያንስ 595 ግራም ብር የሚገዛ የገንዘብ መጠን ያለው ባለሀብት 1/40ኛውን (2.5%) ጠጢ ማድረግ ይጠበቅበታል።</u>

❁❁❁

# 4-የንግድ ዘካህ

ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውም ሸቀጥና ዕቃ ድምር ተመኑ ከላይ የተጠቀሰውን የጥሬ ገንዘብ «ኒሷብ» የሚያክል ከሆነ ዓመት በሞላው ጊዜ ከዋጋው 1/40ኛውን ለዘካህ መውጣት ይኖርበታል፡፡

የንግድ ዘካህን አስመልክቶ ማስተዋል የሚሹ በርካታ ነጥቦች አሉ፦

1. የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በተዘጋጁ ንብረቶች ዋጋ ላይ ብቻ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ለንግዱ ተግባር አጋዥ የሆኑ ማሽኖች፣ ማመላለሻ መኪናዎች፣ ታክሲዎች፣ ለኪራይ የተዘጋጁ ንብረቶችና የመሳሰሉት የዘካ ግዴታ አይመለከታቸውም፡፡ ሆኖም ከነዚህ የሚገኘው የገንዘብ ገቢ ለዘካህ ብቁ ሆኖ ዓመት ከሞላው እንደማንኛውም የዘካህ ንብረት ይታያል፡፡

   ➔ ወደ ሸቀጥነት ተቀይረው ለሽያጭ የሚቀርቡ ጥሬ ዕቃዎች በጥሬ ዕቃነታቸው ዋጋቸው ተተምኖ ዘካህ ሊወጣላቸው ይገባል፡፡

2. የንግድ ዘካህ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በቀረቡት ንብረቶች ድምር ተመን/ዋጋ ላይ እንጂ በንብረቶቹ ራሳቸው ላይ አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት፦

   2.1 እንደ ከብቶችና ወርቅ ያሉ ሌሎች የዘካህ ንብረቶች ለሽያጭ ከቀረቡ የሚመለከታቸው የንግድ ዘካህ ብቻ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ፤ ስለሆነም ዋጋቸው ተተምኖ የንግድ

«ኒሷብ» ከደረሰ 1/40ኛው ወጪ ይሆናል እንጂ ሌላ ግዴታ አይመለከታቸውም።

2.2 በንግዱ ዓለም ለሽያጭ የቀረቡ ንብረቶች እየተሸጡ በሌላ መተካታቸው የተለመደ ነውና ሸቀጦቹ ራሳቸው አመት ሲሞላቸው የግድ አይልም፤ ዘካው የተያያዘው ከሸቀጦቹ ካፒታል/ዋጋ ጋር ነውና።

2.3 የንግድ ዘካህ ሲሰላ ከሌላ ጥሬ ገንዘብ ጋር ተደምሮ መሆን ይገባዋል። ይህ ጊዜውንም (የዘካህ ዓመቱን)፣ መጠኑንም (ኒሷቡንም) የሚመለከት ነው። ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ለዘካህ የደረሰ ጥሬ ገንዘብ በረመዳን ወር ቢያገኝና አመት ሳይሞላው በተወሰነው ገንዘቡ ለንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን ቢገዛ በዘካው ላይ የሚያስከትለው ለውጥ የለም፤ በሚቀጥለው ረመዳን ወር የሸቀጦቹን ድምር ተመን አውጥቶ ከተረፈው ጥሬ ገንዘብ ጋር በማደበል ዘካህ ያወጣል። እንደዚሁም፦ አንድ ሙስሊም ጥሬ ገንዘብና ሌላ የንግድ ሸቀጥ ኖሮት ሁለቱም እያንዳንዳቸው ኒሷብ ያልደረሱ ሆነው የሁለቱ ድምር ኒሷብ ቢሞላ ከድምሩ ዘካህ ማውጣት ይጠበቅበታል።

3. የንግድ ሽያጭ ትርፍ ዘካህ መታሰብ የሚጀምረው ለሽያጭ ከሚቀርበው ሸቀጥ ካፒታል መነሻ ስለሆነ አዲስ የዘካህ አመት አይጀመርለትም።

ለምሳሌ፦ አንድ ባለሀብት በአመቱ መጀመሪያ በ100 ሺህ ብር ሸቀጦችን ሸምቶ ንግድ ቢጀምርና በአመቱ መጨረሻ የ30ሺህ ብር ትርፍ ቢያገኝ ዘካህ የሚያወጣው ከ130 ሺህ ብር ይሆናል። ኪሳራም ቢያጋጥመው

እንዲሁ በአመቱ መጨረሻ ያለውን ንብረት መጠን ተምኖ 1/40ውን ማውጣት ብቻ ነው የሚኖርበት፤ የ100 ሺህ ብር የንግድ ሸቀጥ ገዝቶ በአመቱ ማብቂያ የ20 ሺህ ብር ኪሳራ ቢደርስበት ዘካ የሚያወጣው ከ80 ሺህ ብር ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

▶ በመሆኑም ለሽያጭ የቀረበው ንብረት ዘካህ ሲሰላ የሚታሰበው <u>ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ሳይሆን በዘካው ወቅት የሚሸጥበት ዋጋ መሆኑን ማስተዋል ያሻል</u>።

➔ የንግድ አክሲዮን ባለቤት የሆነ ግለሰብ የአክሲዮኑ ድርሻ የሚወክለውን የሽያጭ ዕቃ ተመንና ትርፍ ከሌላ ጥሬ ገንዘብ ጋር ደምሮ በማስላት ዘካህ ያወጣል፤ ድርጅቱ የአክሲዮኖቹን ዘካህ የሚያወጣ እንደሆነ ግን ግለሰቡ ዳግም ወጪ አይጠበቅበትም።

☸ በመሬት ውስጥ ተቀብሮ የተገኘ የድሮ ቅርስ (ሪካዝ) ቀድሞ የሙስሊም ንብረት እንደነበር የሚጠቁም ምልክት ካለው ለጠፋ ንብረት የሚሰጠው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል፤ ካልሆነ ግን ጥቅል መጠኑ ይነስም ይብዛም 1/5ኛው (20%) ወጪ ይሆናል። ሆኖም የተገደበ የኒሷብ መጠን የሌለው ከመሆኑ፣ ከወጪ አደራረጉና ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር በዘካህ ህግ ስር የማይካተት መሆኑ የብዙሀኑ ሊቃውንት አቋም ነው።

☸ ☸ ☸

# የዘካ አወጣጥን የተመለከቱ ጥቂል ነጥቦች

## 1. ዘካን በየአመቱ ማውጣት

ከአዝርዕት በስተቀር ያሉ የዘካ ንብረቶች ከ«ኒሷብ» እስካልጎደሉ ድረስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየአመቱ የዘካህ ወጪ ይመለከታቸዋል፡፡

## 2. ዘካህና ዕዳ

ዕዳ በዘካህ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተለያዩ አቋም ይዘዋል፡፡ ሆኖም ሚዛን የሚደፋውን አመለካከት መጥቀሱ በቂ ይሆናል፤

2.1 ዕዳ ያለበት ሰው ዕዳውን የሚከፍልበት ጊዜ ካልደረሰ በስተቀር ከዘካህ ሒሳቡ ላይ ዕዳውን አይቀንስም፡፡ ምክንያቱም በእጁ ባለው ገንዘብ መጠቀም እስከቻለ ድረስ ዘካውን የማውጣት ሐላፊነት ስለሚኖርበት ነው፡፡ ዕዳውን የሚመልስበት ወቅት ከደረሰ ወይም ከቀረበ ግን መጠኑን ቀንሶ ሒሳቡን ያሰላል፡፡

2.2 ሌላ ሰው ዘንድ የዕዳ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ደግሞ በፈለገው ጊዜ በእጁ የሚያገኘውና የሚጠቀምበት ባለመሆኑ ገንዘቡ እስኪመለስለት ድረስ ዘካህ የማውጣት ግዴታ አይኖርበትም፤ በአንድ ንብረት ላይ ሁለት ዘካህ አይወጣምና! ሆኖም ገንዘቡ የሚመለስበት ጊዜ ደርሶ ባለዕዳው ዕዳውን ለማስረከብ ዝግጁ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ የዘካህ ሒሳቡ በባለንብረቱ ላይ የሚታሰብ ይሆናል፡፡

3. ዘካህና ወርሀዊ ገቢ

ለዘካህ የደረሰ የንብረት መጠን ኖሮት ዓመት ሳይሞላው ሲሳ ጭማሪ ያገኘ ግለሰብ ያገኘው የንግድ ትርፍ ወይም ከቀድሞ ከብቶች የተወለደ ግልገል እስካልሆነ ድረስ አዲስ የዘካህ ዓመት ይጀምርለታል፡፡

➔ በዚህም መሠረት ገቢውን የሚያጠራቅም ደሞዝተኛ ጥርቅሙ የዘካህ ኒሷብ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ አመት መቁጠር ይጀምራል፡፡ ከዚያ በኋላ በየወሩ የሚያገኘው ደሞዝ ለየብቻው ኒሷብ ባይሞላ እንኳ አመት ሲሞላው 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካህ ወጪ ያደርጋል፡፡

ይህ መንገድ ለእያንዳንዱ ወር አዲስ ሒሳብ በማስላት ከአመት በኋላ በየወሩ ዘካህ ማውጣት ስለሚያስፈልገው አፈፃፀሙ ለብዙዎች አሰቸጋሪ ይሆናል፡፡

➔ ስለሆነም ቀላልና ገር የሆነው መንገድ በአመቱ መጨረሻ ላይ በእጅ ያለውን ገንዘብ ባጠቃላይ በማስላት 1/40ኛውን ማውጣት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የተወሰነው የገንዘብ መጠን አመት ሳይሞላው በቅድሚያ ዘካህ ይወጣለታል ማለት ነው፡፡

# ዘካህ የሚሠጣቸው ወገኖች

የዘካህ ድጎማ የሚገባቸው ወገኖች ስምንት ዓይነት ናቸው:: እነርሱም በሚከተለው የአላህ ቃል ተዘርዝረዋል፦

◄ إِنَّمَا الصَّدَقَاتُ لِلْفُقَرَاءِ وَالْمَسَاكِينِ وَالْعَامِلِينَ عَلَيْهَا وَالْمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمْ وَفِي الرِّقَابِ وَالْغَارِمِينَ وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ وَابْنِ السَّبِيلِ فَرِيضَةً مِنَ اللَّهِ وَاللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ

[التوبة: ٦٠]

►« (ግዴታ) ምፅዋትም ለድሆች፣ ለምስኪኖች፣ በሷም ላይ ሠራዎች ለሆኑ፣ ልቦናቸው (ኢስላምን)የሚላመድ፣ በባሮችም፣ በባለዕዳዎች፣ በአላህም መንገድና፣ (ካገሩ ለወጣ) መንገደኛ ነች፤ ከአላህ ዘንድ (የተገደበች) ግዴታ፤ አላህም እጅግ አዋቂ፣ ጥበበኛ ነው።»

ማብራሪያው እንደሚከተለው ይጠቃሳል፦

1. ድሆች፦ ድሆች የሚባሉት የእለት ጉርሳቸውን በበቂ መልኩ የማያገኙ ናቸው:: ዘካህ ሲከፋፈል ቢቻል የመሥራት አቅም ላላቸው ከድህነት ወጥተው የሚቋቋሙበት፣ አቅሙ ለሌላቸው ደግሞ ለአመት የሚበቃቸውን ያክል ቢሰገሉ ይመረጣል::
2. ምስኪኖች ፦ ምስኪኖች የሚባሉት አስፈላጊ የኑሮ ማሚያዎችን የማያገኙ ናቸው::[1]

(1) በድሃ(الفقير)ና በምስኪን(المسكين) መካከል ያለውን የትርጉም ልዩነት አስመልክቶ በርካታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል።

3. **የዘካህ ሰብሳቢዎችና አከፋፋዮች፦** እነርሱም የሙስሊሞች የበላይ መሪ ዘካህን እንዲሰበስቡና እንዲያከፋፍሉ የመደባቸው ሲሆኑ ለዚህ ስራቸው ከዘካህ ገንዘብ አበል ይቆረጥላቸዋል፡፡

4. **ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመድ፦** እነኚህም ኢስላምን ለመቀበል ዝንባሌ ያላቸው፣ ወይም አዲስ ሰለምቴዎች ሆነው እምነታቸው ያልጠነከረ ግለሰቦች ሲሆኑ የዘካህ መልካም አድራጎት ለእምነታቸው መስተካከልና መሻሻል አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ከተገመተ ከዘካህ ወጪ ውስን ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

5. **በባርነት ሥር ያሉ ሙስሊም ወገኖች፦** በባርነት የሚገዙ ሙስሊሞችን ገዝቶ ነፃ ለማውጣት ወይም በተወሰነ ክፍያ ነፃነታቸውን ለማግኘት ከአሳዳሪዎቻቸው ጋር ውል የፈፀሙትን በክፍያ ለማገዝ ከዘካህ ገንዘብ ወጪ ይደረጋል፡፡

➔አንዳንድ ሊቃውንት ምርኮኛን ለማስለቀቅ የሚከፈል ቤዛ በዚሁ ፍርድ ውስጥ እንደሚካተት ይናገራሉ፡፡

6. **ባለዕዳዎች፦** ዕዳ ተሸክመው መክፈል የተሳናቸው ወገኖች ዕዳቸውን መክፈል የሚችሉበት የገንዘብ መጠን ከዘካህ ይሰጣቸዋል፡፡

ባለዕዳዎች ሁለት ዓይነት ናቸው፤

❶ ለግል ጥቅማቸው ወይም በግል ጥፋታቸው ምክንያት ዕዳ የተጫነባቸው፣

❷ በሰዎች መሀል የሚከሰት ጠብን ለማብረድ የንብረት ዋስትና የተሸከሙ፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የግል ሀብት ቢኖራቸውም ለዘካህ ድጎማ ተገቢ ናቸው፡፡

➔ ሲሳ ሰው ዘንድ በዕዳ መልክ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ዘካህን በመስጠት ዕዳቤ ገንዘብ ሳያወጣ ከባለዕዳው ዕዳን ማቃለል ወይም መሰረዝ የፌስን ጥቅም መጠበቅ ነውና እንደዘካህ አይፈጸድም።

7. **በአሳህ መንገድ ላይ ታጋይ የሆኑ፦** ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ተቆራጭ የሌላቸው ታጋዮች በ«ጂሃድ» የሚያስፈልጋቸው ወጪ ከዘካህ ይሰጣቸዋል። ብዙሀኑ ሊቃውንት ይህ መልዕክት የተጠቀመበት ቁርዓናዊ ቃል (وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ) ሴሎች ሰናይ አድራጎቶችን እንደማያካትት አስረግጠው ይናገራሉ። በዚህም መሥሪት መስጂድ ለመገንባት፣ ት/ቤቶችን ለማቋቋም፣ ጠቃሚ መፅሐፍትን አትሞ ለማሰራጨት፣ የሕክምና ማዕከላትን ለመመሥረትና ለመሳሰሉት የበጎ ተግባር መስኮች የዘካህ ገንዘብን ማዋል የማይፈቀድ ይሆናል ማለት ነው። ሆኖም ብዙ ሊቃውንት ለኢስላማዊ እውቀት ፍለጋ ጊዜያቸውን የሰጡ ተማሪዎች እንደ ታጋዮች የዘካህ ድርሻ እንደሚገባቸው ያስፍራሉ።

8. **ወደ አገሬ የሚመለስበት ወጪ ያጣ መንገደኛ፦** እንዲህ ዓይነቱ በመኖሪያ አገሬ በቂ ሀብት ቢኖረው እንኳ ወደ አገሬ መመለሻ የጉዞ ወጪ ከዘካህ ገንዘብ ይሰጠዋል።

❁ ❁ ❁

## የዘካህ አሰጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

1. ዘካህን ለዘመድ መስጠት፦ ማስተዳደሩ ግዴታ ሳልሆነ ዘመድ ዘካህን መስጠት ይፈቀዳል፡፡ ወጪያቸውን መሸፈን ግድ ለሚል የቅርብ ዘመዶች መስጠቱ ግን ወጪን በማስቀረት እራሱን መጥቀም በመሆኑ የተከለከለ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ለወላጆች፣ ለልጆችና ለሚስቶች ዘካህ መስጠት ይከለከላል፡፡
2. የአሏህ መልዕክተኛ ቤተሰቦችና ዝርያዎች፦ የዘካ ገንዘብን መቀበል አይችሉም፡፡
3. ሙስሊም ሳልሆነ ሰው ዘካህ መስጠት አይቻልም፡፡ ከዘካ ውጪ ያለ ተራ ምፅዋት መስጠት ግን አይከለከልም ፡፡
4. ዘካህ ግዴታ የሆነበት ሰው ወቅቱ ከደረሰ በኋላ በቂ ምክንያት ሳይኖር ማዘግየት የለበትም፡፡
5. የሁለት ዓመት ዘካህ አስቀድሞ ማውጣት እንደሚፈቀድ የሚያሳይ ሀዲሣዊ መረጃ አለ፡፡
6. ዘካህን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ማሻገር፦ ይበልጥ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ እንደሚፈቀድ በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ፡፡

# ተፈጸመ!!

# ዘካተል ፊጥር እና አፈጻጸሙ

## በጣሀ አህመድ

ዘካተል ፊጥር ከረመዳን ወር ፆም መጠናቀቅ ጋር በተያያዘ ግዴታ የሚሆን የዘካ አይነት ነው::ዘካተል ፊጥርን መስጠት እያንዳንዱ ሙስሊም ላይ በነፍስ ወከፍ ግዴታ ሲሆን፤ እያንዳንዱም አባወራ የራሱን ጨምሮ በእርሱ ስር ስላሉ ቤተሰቦቹ ሁሉ መስጠት ይጠበቅበታል:: ኢብኑል ሙንዚር 'አል-ኢጅማዕ' በተሰኘው ኪታባቸው ‹‹**ዒልምን የተማርንባቸው ዑለማዎች ሁሉ ዘካተል ፊጥር ግዴታ መሆኑን ተስማምተውበታል**›› በማለት የጉዳዩን ግዴታነት ከሚያመለክቱት ነብያዊ ሀዲሶች በተጨማሪም የኡለማዎችን አጠቃላይ ስምምነት (ኢጅማዕ) የተገኘበት መሆኑን ጠቁመዋል::

## የተደነገገበት ጥበብ

ድሆች በባዕሉ (ዒድ) እለት ሰዎችን ከመለመን እንዲድኑና የእለቱ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በፆም ወቅት ተከስተው ሳለፉ አንዳንድ ጉድለቶች (ግድፈቶች) ማሟያ እንዲሆን ነው:: ይህን አስመልክቶ ዐብደላህ ኢብን አባስ እንዲህ ይላሉ::

عن ابن عباس - رضي الله عنهما - قال: "فرض رسول الله صلى الله عليه وسلم زكاة الفطر طهرة للصائم من اللغو والرفث وطعمة للمساكين، فمن أداها قبل الصلاة فهي زكاة مقبولة، ومن أداها بعد الصلاة فهي صدقة من الصدقات" رواه أبو داود وابن ماجه

‹‹**የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዘካተል ፊጥርን ለፃመኛ ለ 'ለግዉ'** (ጥቅም ለሌላቸው ውድቅ የቀልድ ንግግሮችና ተግባሮች) **እና ለ 'ረፈስ'** (ፃታዊ ስሜትን ቀስቃሽ ለሆኑ ንግግሮች) **ማፅጃ፤ ለምስኪኖች (ድሆች) ሙብል ሲሆን በግዴታ መልኩ ደንግገውታል:: ስለዚህም ከኢድ ሰላት በፊት (ዘካውን በመስጠት ግዴታውን የተወጣ) ተቀባይነት ያለው ዘካን ሰጥቷል፤ ከኢድ ሰላት በኋላ ዘካውን የሰጠ ከሌላ ግዴታ ያልሆነ ሰደቃ አንዱ እንደሆነ ይታሰብለታል::**›› (አቡዳውድ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)

## የዘካተል ፊጥር መጠን

ኢብኑ ዑመር ሀዲስ ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት ስለተላለፈ ነው **‹‹የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በላቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሷዕ›› በእያንዳንዱ ሙስሊም፤ ባሪያ፣ ጨዋ (ባሪያ ያልሆነ)፣ሴት፣ ህፃን፣ አዋቂ ላይ ግዴታ አድርገዋል:: እንዲሁም ሰዎች ወደ (ዒድ) ሰላት ከመውጣታቸው በፊት ለሚገባቸው ሰዎች እንዲደርስ አዘዋል::››**

(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ሷዕ የመስፈሪያ አይነት ሲሆን በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ነው። በዘመናዊ መለኪያ አንድ ‹‹ሷዕ›› 2.04-2.5 ኪ.ግ ይመዝናል::

1 ሷዕ = 4 የሁለት ዕጅ እፍኞች ነው።

## ዘካተል ፊጥር በማን ላይ ግዴታ ይሆናል?

ዘካተል ፊጥር ግዴታ የሚሆነው ሁለት መስፈርቶችን ባሟላ ሰው ላይ ብቻ ነው፤ እነርሱም

1. ሙስሊም በሆነ
2. ዘካተል ፊጥር ማውጣት ግዴታ በሚሆንበት ቀን እና ሌሊት፤ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ የሚበቃ መብል ኖሮት የተረፈው እና ተጨማሪ ነገር ያለው::

## ዘካተል ፊጥር የሚሰጠው መቼ ነው?

ዘካተል ፊጥርን ከ(ዒድ) ሰላት በኋላ ማዘግየት የተከለከለ ሲሆን፤ ማውጣቱ ግዴታ የሚሆንበት ወቅት የሚጀምረው ከረመዳን የመጨረሻው እለት ፀሀይ ከጠለቀችበት ወይም ዒድ መሆኑ ከተረጋገጠበት ሰዓት አንስቶ ነው:: ነገር ግን ኢብኑ ዑመርን ጨምሮ ሌሎቹም ሰሀቦች ያደርጉት እንነበረው ከዒድ አንድ ወይም ሁለት ቀን ቀድሞ ዘካተል ፊጥርን ማውጣት ይፈቅዳል::

## ሰዎች ለዘካተል ፊጥር የሚሰጡ የእህል አይነቶች

ዘካተል ፊጥር ሙስሊሞች ከሚመገቡዋቸው እንደ እሩዝ፤ በቆሎ፤ ጤፍ.... ባሉ የምግብ እህል አይነቶች ነው። መልእተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) በሀዲስ የጠቀሷቸው የምግብ እህሎች (እንደ ገብስ፤ ተምር፤ ዘቢብ) የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ነገር ግን የምግብ አይነቶቹ በነዚህ ላይ ብቻ እንደማይገደቡ የሻፊዒያ እና የማሊኪያ መዝሀብ ዑለማዎች ሲስማሙበት ሸይኹል ኢስላምም የመረጡት አቋም ነው::

የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሷዕ›› እንዲወጣ ማዘዛቸውን በተመለከተም እነዚህ ዑለማዎች የሚሰጡት ምላሽ ‹‹**መልእክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እነዚህን የምግብ አይነቶች የጠቀሱት የመዲና ሰዎች በምግብነት ይጠቀሟቸው የነበሩ ከመሆናቸው አንፃር ነው:: ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አነሱ የሚያገኙትንና የሚመገቡትን የምግብ አይነት ነው እንዲያወጡ ያዘዟቸው**›› የሚል ነው:: በዚህም መሰረት በማንኛውም አካባቢ የሚኖር ሙስሊም ማህበረሰቡ አዘውትሮ ከሚመገባቸው የምግብ እህሎች ዘካተል ፊጥሩን መልዕክተኛው ሲጠቀሙበት በነበረው መስፈርያ መጠን ማውጣት ይችላል::

## ዘካተል ፊጥር መሰጠት የሚገባው ለማን ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ ዑለማዎች ሁለት አይነት አመለካከት ያለቸው ሲሆን ሚዛን የሚደፋው ሀሳብ ለምስኪኖች እና ለድሆች ብቻ ይሰጣል የሚለው ነው:: ምክንያቱም በኢብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ‹‹**ለምስኪኖች መብል** ...›› በማለት ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ከመግለፃቸው ጋር የተያያዘ ነው::

# ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ ተምኖ መክፈል

ዘካተል ፊጥርን በዋጋ ተምኖ መክፈል አይፈቀድም። ምክንያቱም በኢብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (**የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን**) ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ሲገልፁ ‹‹**ለምስኪኖች መብል ...**›› በማለታቸው ጋር የተያያዘ ነው:: አቢ ሰዒድ አልኹድሪይ እንዲህ ብለዋል “የአላህ መልዕክተኛ በነበሩበት ዘመን ዘካተል ፊጥር የምናወጣው ከምግብ አንድ ሷዕ ነበር” ብለዋል። ዘካተል ፊጥርን ከተገደበለት ጊዜ ማስቀደም ወይም ማቆየት እንደማይቻል ሁሉ የአወጣጡን አይነትም መቀየር አይቻልም። ዒባዳ ሁልጊዜ በአላህ የሚደነገግ እንጂ በአስተያየት ምንፈፅመው አይደለም።ማንኛዉም ሙስሊም ዒባዳው እንዳይበላሸበት ሊጠነቀቅ ይገባዋል። በገንዘብ መተመን በቀደምት ሰለፎች አልተፈፀመም።ከጥቂቶች በቀር አብዛኞቹ የኢስላም ሊቃዉንት በገንዘብ ማዉጣትን ይቃወማሉ። አል-ኢማም ማሊክ፣ አል-ኢማም አሻፊዒይ እና አል-ኢማም አህመድ ይህ መዝሀባቸው ነው። ስለዚህም በተባለው መልኩ በእህል ያወጣ ሰው በሁሉም ስምምነት ትክክለኛ ዒባዳ ሰርቷል። አያንዳንዱ ሙስሊም በፆመበት ቦታ ዘካተል ፊጥርን ማዉጣቱ ቢሆንም የሚያስፈልገው ነገር ግን ምግብ የሚቀበል ሚስኪን ሰው የሌለበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በቤተሰቦቻቸዉ ወይም ጓደኞቻቸው አማካኝነት ችግረኞች ወዳሉበት ቦታ መላክ ይችላሉ። በጥቅሉ ማንኛዉም ሰው ኢስላምን በሚገባ ለመተግበር መሞከር ይገባዋል።

تقبل الله الصّيام والقيام وجميع الطّاعات